# የኢትዮጵያ የደን ልማት

# 2015 በጀት ዓመት የተሻሻለ ዕቅድ

ነሃሴ 2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ማውጫ

1. መግቢያ ..... 2
2. ድርሞ (EXECUTIVE SUMMARY) ..... 3
3. ርዕይ ..... 3
4. ተልዕኮ ..... 3
5. እሴቶች ..... 3
6. መሰረታዊ አቅጣጫዎች ..... 4
7. የዕቅድ ዝግጅት ሂደቶች ..... 4
8. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎቸ ..... 7
9. የትኩረት መስኮች እና ስትራቴጂያዊ ግቦች ..... 8
10. የዋና ዋና ግቦች ትንተና ..... 10
11. ተቋማዊ የለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ (የሪፎርም ሥራዎች) ..... 18
12. ማስፈፀሚያ በጀት ..... 18
13. የክትትልና ግምገማ ስርዓት ..... 20
14. ማጠቃለያ ..... 20
15. ዝርዝር የውጤት አመላካቾችና ዒላማዎች (የድርግት መርሃ ግብር) ..... 21
16. ዕዝል ..... 32

## 1. መግቢያ

የደን ሀብት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጥቅሞችንና ግልጋሎቶችን የሚያበረክት ሀብት ነው፡፡ ደን ለማገዶ እና ለኮንስትራክሽን፣ የቤተሰብ ገቢን እና የሀራችንን ኢኮኖሚ ለማሳደግ፣ የአፈር ክለት ለመቀነስና ለምነትን ለመጨመር፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም፣ ለዱር እንስሳት መጠለያነት፣ በውሀ አካላት ላይ የሚፈጠረውን ደለል ለመቀነስ፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ወዘተ የሚያበረክታቸው አስተዋጽኦዎች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ እያደገ ከመጣው የህዝብ ብዛት ጋር ተያይዞ በደን ውስጥ የህገወጥ እርሻ መስፋፋት፣ ለማገዶ እና ለግንባታ ስራ የሚያገለግል የእንጨት ፍላጎት መጨመር፣ የደን ምንጣሮና የደን ቃጠሎ፣ ልቅ ግጦሽ፣ እንዲሁም በየጊዜው የሚወጡ የህግ ማዕቀፎች በሚፈለገው መጠን ተግባራዊ አለመሆን፣ የመሬት ፓሊሲና ዕቅድ አለመኖር ወዘተ ለደን ሃብታችን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያቶች ናቸው፡፡

መንግስት የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት ለዘርፉ ባለፉት ዓመታት ከምንጊዜውም የበለጠ ትኩረት በመስጠት በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ከእነዚህም ተግባራት መካከል የአስር ዓመት፣ የአምስት ዓመትና ዓመታዊ ዕቅዶች በማቀድ እና የተለያዩ ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን በመቅረጽ የታቀዱ እቅዶች በመተግበር ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ኢኮኖሚያችንን ለማሳደግ፣ የመሬት መራቆትን፣ የበረሃማነት መስፋፋትን፣ የብዝሀ ሕይወት መመናመንን፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የሚኖረንን ተጋላጭነት ለመቀነስና የውሀ ሀብት መጠንና ጥራት ለማሻሻል በክቡር ጠ/ሚኒስትራችን የተጀመረው ሀገራዊ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከሚመለከታችው አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ በዚሁ ፕሮግራም በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሀይማኖት ተቋማት ጭምር እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

## 2. ድርሞ (Executive Summary)

የኢትዮጵያ የደን ልማት የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ሀገራዊ የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ፣ መሰረት በማድረግ፣ የዘርፉን የ2014 በጀት አመት አፈጻጸም በመገምገም ለቀጣይ ዓመት የሚደረስባቸዉን ግቦች ከሀገራዊ የልማት እድገት የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ዘላቂ ልማት ግቦችና፣ የአፍሪካ አጀንዳ 2063 እና አለም አቀፍ ስምምነቶች እንዲሁም አለም አቀፍ፣ አህጉራዊና ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማስተሳሰርና በማጣጣም የተዘጋጀ ነው፡፡ ዕቅዱ የዘርፉን ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች፣ ስትቴጂያዊ ግቦች እና የማስፈፀሚያ እርምጃዎች፣ የፋይናንስ ዕቅድ እንዲሁም የዕቅድ ትግበራ ክትትልና ግምገማ ስርዓትን የያዘ ነው፡፡

## 3. ርዕይ

በ2022 ዓ.ም. ዘላቂ ደን ልማት፣ አያያዝና አጠቃቀምን በማረጋገጥ በአፍሪካ የላቀ የደን ልማት ተቋም ሆኖ መገኘት፡፡

## 4. ተልዕኮ

የደን ሀብታችን በዘላቂነት እንዲጠበቅ፣ እንዲለማ፣ የተራቆቱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ እና የደን ውጤቶችን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ አገራችን ከደን ሀብት የተሻለ ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊ እና ስርዓተ-ምህደራዊ ጠቀሜታን እንድታገኝ በማድረግ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖን በመቋቋም ለሁለንተናዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግ፡፡

## 5. እሴቶች

- ግልጸኝነት
- ቁርጠኝነት
- አጋርነት
- ጥራት
- ቅልጥፍና
- ውጤታማነት
- የሙያ ስነ-ምግባር
- ፈጠራ

## 6. መሰረታዊ አቅጣጫዎች

- ቀጣይነት ያለው አሰራር በተቋሙ ማጠናከር፣
- የተገልጋዮችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የተቋሙን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም በመገንባት የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናን ማጐልበት፣
- የሴቶችንና የወጣቶችን ብቃት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣
- የደን ሃብት ልማት፣ ጥበቃ፣ እንክብካቤና አጠቃቀም ተግባራትን ማጠናከር፣
- የተገልጋይ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ ችግር ፈቺ የደን ምርምር ስራዎችን ማከናወን፣

## 7. የዕቅድ ዝግጅት ሂደቶች

### 7.1. የውስጣዊና ውጪያዊ ሁኔታዎች ትንተና

የታቀዱ ግቦችን ለማሳካት በአፈፃፀም የታዩትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች፣ መልካም አጋጣሚዎች እና ስጋቶች /ፈተናዎች/ ትንተና እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡

#### 7.1.1. የውስጣዊ ሁኔታዎች ትንተና (ጠንካራና ደካማ ጎኖች)

**ጠንካራ ጎኖች**

- የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘት የሚያስችሉ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀትና ተቋማዊ አቅም መገንባቱ፣
- ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከልማት አጋሮችና ከሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ያለው ቅንጅታዊ ትስስርና አጋርነት እየተሻሻለ መምጣቱ፣
- የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማጎልበት በደን ፖሊሲ፣ ህጎችና ስትራቴጂዎች ላይ በተለያዩ ስልቶች የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማጎልበት መቻሉ፣
- ለዜጎች የሚፈጠረው የስራ ዕድል እያደገ መምጣቱ፣
- ሀገራዊ የደን ሃብት መረጃ ይፋ መሆኑ፣
- ለደን ልማት ጉልህ ሚና የሚኖራቸው ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መዘጋጀታቸው፣
- በዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ድርድር መድረኮች እና ፎረሞች ላይ የሀገራችንን ፍላጎት ለማንፀባረቅና ጥረት መደረጉ፣
- ዘመናዊ የምርምር ፋሲሊቲዎች (የላብራቶሪና ግሪን ሀውስ) ግንባታ መጀመሩ፣
- የደን ልማትን ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለማከናወን ሞዴል ችግኝ ጣቢያዎች ለማቋቋም ጅምር ስራዎች መኖሩ፣
- በደን ምርምር የተለያዩ ልምዶችና ማዕከላት መኖራቸው፣

**ደካማ ጎኖች**

- የወጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ህጎችን ለመተግበር የሚያስችል የአቅም ውስንነት፣
- በደን ምርምር የወጡ መረጃና ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ ውስንነት መኖሩ፣
- የግሉ ዘርፍ እና የተደራጁ ማህበራት በደን ልማትና ግብይት ተሳትፏቸው ውስን መሆኑ፣
- ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል ቢሮዎች የክትትል፣ ግምገማና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት የተጠናከረና ወቅታዊ አለመሆኑ፣
- የደን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ስርዓተ-ምህዳራዊ ጠቀሜታን አጉልቶ ማሳየት ላይ ውሱንነት መኖሩ፣
- የግዥ አግልግሎት ወቅታዊና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ አለመፈፀሙ፣

## 7.1.2. የውጨያዊ ሁኔታዎች ትንተና (መልካም አጋጣሚዎች እና ስጋቶች /ፈተናዎች/)

**መልካም አጋጣሚዎች**

- መንግስት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት እያደገ መምጣቱ፣
- ሊያሠሩ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች መኖራቸው፣
- ሊስፋፉ የሚችሉ መልካም ተሞክሮዎች መኖራቸው፣
- የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ትኩረት ማግኘቱ፣
- የሀገራችን ተለያይነት ያለው ስርዓተ-ምህዳር እና ብዝሃ ህይወት መኖር በተለይ የደን ዕፅዋትን ለማልማት እና ምርቱንም በብዛት ለሀገር ውስጥ እና ለዓለም ገበያ ለማቅረብ ከፍተኛ የሆነ እምቅ አቅም መኖሩ፣
- በመንግስት የሚሰሩ ሜጋ የኃል- ማመንጫ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፣
- በመንግስት የሚሰሩ የገጠርና የከተማ መንገድ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፣
- የደን ልማት በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚመጣውን ተፅዕኖ ለመቀነስ ያለውን ሚና በተመለከተ የህብረተሰቡ ግንዛቤ እያደገ መምጣቱ፣
- የሃገሪቱን የደን ሃብት ለማልማትና ለመጠበቅ የሚያስችሉ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ስምምነቶች እና ሃገራዊ ቃል የተገቡ ፍላጎቶች መኖራቸው፣
- የአየር ንብረት ለውጥ የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ የትኩረት አቅጣጫ በመሆኑ በደን ዘርፍ የሚደረጉ ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች ከፍተኛ ሀገራዊ አስተዋፅኦ ያላቸው መሆኑ፣
- በሃገር ውስጥና በአለም አቀፍ ደረጃ ለደን ውጤቶች ያለው ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱ፣
- የጎላ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት መኖራቸው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## ስጋቶች

- የክልሎች ተቋማዊ አደረጃጀት ወጥነትና ተናባቢነት የሚጎለውና ከፌደራል እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- የደን እሳት፣ በሽታ፣ ተባይና መጤ ወራሪ ዝርያዎች መከሰትና ይህን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሀገራዊ አቅምና አደረጃጀት በሚፈለገው ደረጃ ያለመኖር፣
- በየደረጃው ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፣
- የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ መጨመር፣ የተፈጥሮ ደን መመናመንና የበረሃማነት መስፋፋት፣
- የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ አለመኖር፣
- የሃብት ውሱንነት እና የዋጋ ግሽበት፣
- አለም አቀፍ የሰላምና ፀጥታ ችግር/ አለመረጋጋት፣

## 7.2. የ2014 በጀት ዓመት የስራ አፈፃፀም ግምገማ

የኢትዮጵያ የደን ልማት ሃገራዊ ተልዕኮውን ለማሳካት በደን ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲሁም በደን ምርምር ዘርፎች በርካታ ስራዎችን በመፈፀም ላይ የሚገኝ ተቋም ሲሆን የ2014 የበጀት ዓመት የተቋሙ የፊዚካል ስራዎች አፈጻጸም በመቶኛ 91.99 ሆኗል፡፡

የበጀት አፈፃፀሙም በበጀት ዓመቱ ለተቋሙ ከታቀደው መደበኛና ካፒታል በጀት ብር 481,400,378.00 ውስጥ 335,247,989.00 ብር ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ በመቶኛ 69.6 ሲሆን ለተቋሙ ከተለቀቀው መደበኛና ካፒታል በጀት ብር 345,152,128.00 አንፃር 337,347,930.00 ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም በመቶኛ 97.1 ነው፡፡

- በደን ልማትና ጥበቃ እንዲሁም እንክብካቤ ዙሪያ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ከማስፋት አንጻር ለ439,573 (ሴት 147,195) ለሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች በህግ ተከባሪነት ዙሪያ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም በደን ላይ የሚደርሰውን ህገ ወጥ ተግባራትን መከላከልና መቆጣጠር እንዲያስችል በደን ውጤቶች ንግድ ለሚሰማሩ 100 ግለሰቦች/ባለሀብቶች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

- የአገራዊ የደን ሽፋንን ለማሳደግ ይቻል ዘንድ 0.8 ሚልዮን ሄ/ር የተከላ መሬት በመለየትና ደረጃቸውን የጠበቁ 4 ቢልዮን ችግኞች ተፈልተው እንዲተከሉ ለማድረግ ታቅዶ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በተደረገው የመስክ ክትትልና ድጋፍ 3.26 ቢሊዮን የደን ችግኞች በ699,281.05 ሄ/ር ላይ ተከላ ማካሄድ ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ በ67,578.9 ሄ/ር ላይ የተተከለው 42,111,161 የቀርከሀ ችግኝ ነው፡፡

- 19.2 ሚሊዮን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ስራ ለማከናወን ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡ 1 ሚ/ሊ ሄ/ር የተራቆቱ ደኖችና መሬቶችን የመለየት፣ የመከለልና የማልማት ሥራ ታቅዶ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በተደረገው የመስክ ክትትልና ድጋፍ በድምሩ 691,654.4 ሄ/ር (69.2%) ማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ በደን ሴክተር ትራንስፎርሜሽን ዩኒት 3766 ሄ/ር፣ በደን ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራም 177,069 ሄ/ር፣ በከፍታማ ቦታዎች የአየር ንብረት ለዉጥ ማጣጣሚያ ፕሮጀክት 1,419.3 ሄ/ር የተከናወነ ነው፡፡
- በ2.283 ሚ/ን ሄ/ር መሬት ላይ የሚገኙ የተፈጥሮ ደኖችን አሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓትን በመተግበር በዘላቂነት እንዲጠበቁና ተገቢውን ግልጋሎት እንዲሰጡ ለማድረግ 187,383 (ሴት 47,889) አባላት ያሉት 1,152 ማህበራት እንዲመሰረቱ በማድረግ ደኑ ወደ አሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት እንዲገባና ተገቢዉን ጥቅም እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡
- ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የቀረበ የደን ምርትን በተመከተ 1.02 ሚልዮን ቶን የደን ምርት ውጤቶች ለማቅረብ እቅድ ተይዞ 2.134 ሚልዮን ቶን የቀረበ ሲሆን አፈፃፀሙ >100% ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 18,379 ቶን የደን ምርት ውጤቶች ወደ ውጭ ሀገር በመላክ **2.3803** ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ተችሏል፡፡
- የስራ ዕድል ፈጠራን በተመለከተ ለ0.25 ሚሊየን ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ255,506 (ሴት 72,299) ለሚሆኑ ዜጎች በዘርፉ ጊዜያዊ እና ቋሚ ስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡
- በምርምሩ ዘርፍ በበጀት ዓመቱ 50 የምርምር ውጤቶችን (41 መረጃዎች እና 9 ቴክኖሎጂዎች) ለማውጣት ታቅዶ 37 ውጤቶች (31 መረጃዎች እና 6 ቴክኖሎጂዎች) ወጥተዋል፡፡

በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ቢኖሩም ተቋሙ እነዚህን ችግሮች ባለው ውሱን ሃብት እና የሰው ሃይል ተረባርቦ በመስራት ስራዎችን በዕቅድ መሰረት ለመፈፀም ተችሏል፡፡

## 8. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች

የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ሲዘጋጅ ቀጥለው የተዘረዘሩትን መነሻ ሀሳቦች ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

- ሀገራዊ የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ፣
- የተቋሙ 10 ዓመት (2013-2022) እና የ5 ዓመት (2013-2017) ዕቅድ፣
- የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ግብረ-መልስ፣
- የ2014 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ፣
- የ2015 በጀት ዓመት ለተቋሙ የተፈቀደ በጀት፣

- ብሄራዊ የደን ዘርፍ የልማት ፕሮግራም፣ የደን ምንጣሮና መመናመን የሚለቀቅ የሙቀት አማቂ ጋዝ ቅነሳ ስትራቴጂ (REDD+)፣ የቀርከሃ ስትራቴጂ፣
- ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራተጂና የክትትልና ግምገማ ስርዓት፣
- በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የተከለሰ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ (Updated NDC)፣
- የኦዲት ግኝት (የፋይናንስና ክዋኔ ኦዲት)፣
- የኢትዮጵያ የደን ልማትን ስልጣን፣ ተግባርንና አደረጃጀትን ለመወሰን የወጣ ደንብ፣
- የደን ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች፣ የአፍሪካ አጀንዳ 2063 እና አለም አቀፍ ስምምነቶች

## 9. የትኩረት መስኮች እና ስትራቴጂያዊ ግቦች

### የትኩረት መስኮች

ተቋሙ በህግ የተሠጠውን ስልጣንና ተግባር፣ ያሉትን እሴቶች፣ ጥንካሬዎች እና ድክመቶች፣ መልካም አጋጣሚዎችንና ስጋቶችን በመተንተን የሚከተሉት ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች ተለይተዋል::

ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች

1. ዘላቂ የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና አጠቃቀም፣
2. ችግር ፈቺ የደን ምርምር፣
3. ተቋማዊ አቅም ግንባታ፣
4. የደን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስርዓተ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ፣
5. የአረንጓዴ አሻራ ስራዎች፣

## ስትራቴጂያዊ ግቦችና ክብደት

| ዕይታ | ስትራቴጂክ ግቦች | ክብደት በ% |
|---|---|---|
| ተገልጋይ (20%) | ግብ 1. የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ | 20 |
| ፋይናንስ (15%) | ግብ 2. የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ | 10 |
| | ግብ 3. የሀብት ግኝትን ማሳደግ | 5 |
| የውስጥ አሰራር (40%) | ግብ 4. ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ጤታማነት ማሻሻል | 6 |
| | ግብ 5. የደን ህግ ተከባሪነት ማጎልበት | 5 |
| | ግብ 6. አገራዊ የደን ሽፋንን ማሳደግ ፣ | 7 |
| | ግብ 7. የደን ሃብት ለኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ ማሳደግ፣ | 5 |
| | ግብ 8. የመረጃና ቴክኖሎጂ ማመንጨትና ማላመድ | 7 |
| | ግብ 9. የመረጃና ቴክኖሎጂ ትውውቅና ሽግግርን ማሳደግ | 5 |
| | ግብ 10. የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ | 5 |
| መማርና እድገት (25%) | ግብ 11. የዘርፉን የመሰረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ፣ | 15 |
| | ግብ 12. የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ፣ | 10 |

## በዝግጅት ምዕራፍ የሚሰሩ ስራዎች

የዝግጅት ምዕራፍ ተቋሙ የተቋቋመለትን አላማ እና ተልዕኮ ለማሳካት በበጀት ዓመቱ ሊከናወኑ የሚገባቸው ስራዎች የሚለዩበት፣ መርሃ ግብር የሚዘጋጅበት፣ ግብዓት የማሟላት ስራዎች የሚከናወኑበት እና ለትግበራ የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች የሚደረጉበት ምዕራፍ ሲሆን በዚህ ወቅት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የ2014 በጀት ዓመት የተቋሙን የስራ አፈፃፀም መሰረት በማድረግ የ2015 በጀት ዓመት ፋይናንስና የፊዚካል ስራዎች ዕቅድን አሳታፊ በሆነ መንገድ ማዘጋጀት፣ የሥራ ክፍሎች እቅዱን እስከ ፈፃሚ እንዲያወርዱ ማድረግ፣ ለባለድርሻ አካላት ማስተዋወቅ፣
- ለዕቅዱ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማሟላት፣
- ለዕቅዱ ተፈፃሚነት የሚያግዙ የውስጥ አሰራር መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣ መከለስና ወደስራ ማስገባት ናቸው፡፡

**በትግበራ ምዕራፍ የሚሰሩ ስራዎች**

የትግበራ ምዕራፍ በተቋሙ የተለዩትን የትኩረት መስኮችን መሰረት በማድረግ በዕቅድ የተያዙትን ግቦች እና ግብ ተኮር ተግባራትን ለማሳካት ተገቢውን ጥረት ማድረግ፣ ስራዎችን በዕቅድ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ፣ መጠን እና በሚፈለገው የጥራት ደረጃ በውጤታማነት መፈፀም፣ አፈፃፀሙንም በየደረጃው መከታተልና መገምገምና መደገፍ፣ ክፍተቶች ሲያጋጥሙ የማስተካከያ እርምጃ በወቅቱ መውሰድ የመሳሰሉት ዋና ዋና ስራዎች የሚተገበሩበት ምዕራፍ ነው፡፡

## 10. የዋና ዋና ግቦች ትንተና

**ግብ 1 የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ**

የሚጠበቅ ውጤት፡ ያደገ የተገልጋይ ዕርካታ

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎቶች መስጠት፣
- የተገልጋይ እርካታ ከ 84 % ወደ 90% ማሳደግ፣
- በአገልግሎት አሰጣጥ የሚነሱ ቅሬታዎችን በመከታተል 100% ምላሽ መስጠት፣
- የተገልጋይ እርካታን ደረጃ ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣

**ግብ 2 የሃብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ፣**

የሚጠበቅ ውጤት፡ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ መሰረት 100% በጀት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣
- በ2013 የፌደራል ዋና ኦዲት የፋይናንስ እና የንብረት ኦዲት ግኝት ላይ የማስተካከያ የእርምት እርምጃ በመውሰድ 100% ማከናወን፣
- የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ሥርአት ብቃት ያለው መሆኑን በየጊዜው በመገምገም የሚሻሻልበትን ሁኔታ በመፍጠር ከስጋት ነፃ የሆነ የውስጥ ቁጥጥር ሥርአት መዘርጋት፣
- 2015 በጀት ዓመት የውስጥ ኦዲት ማድረግ፣
- በ2014 በጀት ዓመት በፌደራል ዋና ኦዲተር በተከናወነው የፋይናንስ ኦዲት ግኝቶች መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ የማስተካከያ መርሃ ግብር አፈፃፀም መከታተል፣

**ግብ 3 የሃብት ግኝት ማሳደግ**

የሚጠበቅ ውጤት፡ ያደገ ተቋማዊ ሃብት

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ከአጋር ሀገሮች እና ድርጅቶች 30 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲሰበሰብ ማድረግ፣
- ከዛፍ ዘርና ተረፈ ምርት ሽያጭ 1 ሚ/ብር መሰብሰብ፣

**ግብ 4፡- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል**

የሚጠበቅ ውጤት፡ የተሻሻለ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራ

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- 7 ሚሊየን ቶን ከደን ዘርፍ  የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት መጠን መቀነሱን ማረጋገጥ፣
- የደን ሽፋን መለካትና መረጃ ማውጣት፣
- በአለም አቀፍ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ መድረኮች በመሳተፍ የሃገሪቱን የደን ጥቅም ማስጠበቅ፣

**ግብ 5፡-የደን ህግ ተከባሪነት ማረጋገጥ፣**

የሚጠበቅ ውጤት፡ የተሻሻለ የደን ህግ ተከባሪነት፣

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የህግ ማስፈፀሚያ ማዕቀፎች ማዘጋጀት፣
- በደን ህጎች እና አፈፃፀም ላይ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተለያዩ ዘዴዎች ግንዛቤ መፍጠር፣
- በደን ሃብት ላይ የሚደርሱ ዋና ዋና ጥፋቶችና ህገወጥ እንቅስቃሴዎች ያለባቸውን  አካባቢዎች መለየት፣
- በደን ዘርፍ ለሚሰማሩ 400 ባለሀብቶች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፣

**ግብ.6 - አገራዊ የደን ሽፋንን ማሳደግ**

የሚጠበቅ ውጤት፡ ያደገ ሀገራዊ የደን ሽፋን

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 19.2 ሚሊዮን ሄ/ር ነባር፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ደን እንዲጠበቁ መደገፍ፣
- የተተከሉ ችግኞችን አማካይ የፅደቀት ምጣኔ 85 በመቶ ለማድረስ መደገፍ፣
- አንድ ሚሊዮን ሄ/ር የተራቆተ የደን መሬት እንዲለዩ፣ እንዲከለሉ እና እንዲለሙ ድጋፍ ማድረግ፣
- በደን የተሸፈነ መሬት ከ17% ወደ 20% ማሳደግ

- 0.6 ሚሊዮን ሄ/ር ለተከላ የሚሆን ቦታ እንዲዘጋጁ ድጋፍ ማድረግ፣
- 200 ቶን የዛፍ ዘር የማሰባሰብና የማሰራጨት ስራን መደገፍ፣
- የዛፍ ዘር ዕጥረት ያለባቸውን እና ወደ ዛፍ ዘር ስርዓት ያልገቡ 15 የዛፍ ዝርያዎችን ዘር ወደ ዛፍ ዘር ስርዓቱ እንዲገቡ ማድረግ፣
- 3 ቢሊዮን የዛፍ ችግኞች እንዲዘጋጁ ድጋፍ ማድረግ፣
- በ0.02 ሚሊዮን ሄ/ር ላይ የቀርቀሀ ደን እንዲለማ መደገፍ፣
- ሀገራዊ የደን ሀብት ቆጠራ ሥራን 50% ማከናወን፣
- ለ0.2 ሚሊዮን ሄ/ር ደን ማኔጅመንት ፕላን ማዘጋጀት፣
- ለ5 ከተሞች የደን ልማትና አያያዝ እንዲሻሻል መደገፍ፣
- 100 ሺህ ሄ/ር ላይ የጥምር ደን ግብርና ስራ እንዲካሄድ መደገፍ፣
- የደን እሳት መንስኤዎችን ለመለየት፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያና መከላከያ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችሉ ሁለት ማንዋሎችን ማዘጋጀት፣
- በ4 ክልሎች የደን እሳት ቃጠሎ ለመቆጣጠር እንዲቻል ግብረ ሃይል እንዲደራጅ እና እንዲጠናከር ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፣
- የደን መጤ እና ወራሪ ዝሪያ አረሞች መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ማንዋል ማዘጋጀት፣
- በደን ተባይ በሽታ የቅድመ መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ማንዋል ማዘጋጀት፣
- የደን ማኔጅመንት ፕላን ዝግጅት መመሪያ (Guideline) ማዘጋጀት፣

**ግብ 7. የደን ሀብት ለኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ ማሳደግ፣**

የሚጠበቅ ውጤት፡- ያደገ ሃገራዊ የኢኮኖሚ ድርሻ

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- 2.16 ሚ/ሄ/ር ነባር የተፈጥሮ ደን በአሳታፊ ደን አስተዳደር ስርዓት ውስጥ መሆናቸውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- 0.2 ሚ/ሄ/ር አዲስ የተፈጥሮ ደን በአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት እንዲካተቱ ማድረግ፣
- 250 ሚሊዮን ብር ከሮያሊቲ ክፍያ እዲሰበሰብ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- 0.25 ሚሊየን ዜጎች የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ድጋፍ ማድረግ፣
- ኑሮአቸውን በዘርፉ ላይ መሰረት ያደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማጥናት፣
- 0.2 ሚሊ/ቶን ከሰል ከሰው ሰራሽ ደንና ከደን ተረፈ ምርቶች በተሻሻለ ዘዴ እንዲመረት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- 1.02 ሚሊ/ቶን የደን ምርት ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

- ከደን ምርት ውጤት ኤክስፖርት እና በሃገር ውስጥ በሚመረት የደን ምርት ውጤት ምክንያት የውጪ ምንዛሬን በማዳን 20 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲገኝ ማድረግ፣
- የደን ሃብት ለሃገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ማስጠናት፣
- የደን ኢንተርፕራይዞችን እና ኢንዱስትሪዎችን ያለባቸውን ችግሮች መለየትና መደገፍ፣

**ግብ 8. በደን ምርምር ቴክኖሎጂና መረጃ ማመንጨት**

**የሚጠበቅ ውጤት፡- በምርምር የወጡ 6 ቴክኖሎጂዎች እና 42 መረጃዎች**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

**በሰው ሰራሽና ጥምር ግብርና ደን ምርምር**

- የኦሜድላ እና የዲክረንስ ግራር መሠረት ባደረገ የጥምር ደን ግብርና ሞዴል ላይ አንድ መረጃ ማውጣት፣
- የማህብረተሰቡን የፍራፍሬ ዛፍ ፍላጎት የመለየት ጥናት መረጃ ማውጣት፣
- 20 የጥምር ደን ግብርና አሰራሮችን የሚያሻሽሉ የምርምር ስራዎች ማከናውን ፣
- ለጣዉላ በሚዉሉ የሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎች የመትከያ ርቀት በመጀመሪያ የእድገት መጠን ላይ ያለዉን አስተዋጽኦ በማጥናት 2 መረጃዎችን ማውጣት፣
- የነጭ ባህር ዛፍ የመትከያ ርቀት በእድገት መጠን እና በእንጨት ባህሪይ ላይ ያለውን ተጽዕኖ በማጥናት አንድ መረጃ ማውጣት፣
- የቀረሮ ዛፍ በቁርጥራጭ ስለሚባዛበት ዘዴ አንድ መረጃ ማውጣት፣
- የጥቁር እንጨት እድገት ሙከራ ማካሄድ፣
- የማህበረሰብ የችግኝ ፍላጎትን በአይነት እና በመጠን የመለየት እና የችግኝ ጣቢያ አሰራር ጥናት 3 መረጃ ማውጣት፣
- ለ24 የሰው ሰራሽ ደን የምርምር ስራዎች የክትትል እና እንክብካቤ ስራዎች ማከናውን፣
- በተራቆቱ እርጥበት አጠር መሬቶች የችግኝ እድገትን ሊያሻሽል የሚችሉ የአተካከል ዘዴዎች ላይ አንድ መረጃ ማውጣት፣
- ውርጭ በሚበዛባቸው ከፍተኛ ቦታዎች ላይ የችግኝ አፀዳደቅ 3 ሙከራዎች ማቋቋም፣
- በወንዝ ዳርቻ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥናት መረጃ ማውጣት፤
- በወንዝ ዳርቻ የሚገኙ የዛፍ እና የቁጥቋጦ ዝርያዎችን ስብጥር ጥናት መረጃ ማውጣት፤
- ለ9 በዛፍ የታገዘ የተፋሰስ አያያዝ እና የተጎዱ መሬቶች ማገገሚያ አያያዝ የምርምር ስራዎችን ማከናወን፣

**በደን አጠባበቅ ምርምር**

- የፈረንጅ ጽድ፣ ቀርከሃ፣ ሞሪንጋ እና የአኬሺያ ዲከረንስን የሚያጠቁ የነፍሳት ተባይ ላይ የምርምር ስራዎችን ማካሄድ፣
- በ3 የዛፍ ዝርያዎች ላይ የሚከሰቱ በሽታዎች ላይ የምርምር ስራዎችን ማካሄድ፣
- የተፈጥሮ ደን ቦታዎች ላይ የእሳት ቀጠና፣ ባሕርይ እና ጸባይ/ሁኔታ ለማወቅ ምርምር ማካሄድ፣

**በዛፍ ዘር ቴክኖሎጅ ምርምር**

- በላቦራቶሪ እና በችግኝ ጣቢያ የዘር ባህሪ ትንተና በማካሄድ መረጃ ማውጣት፣
- 2 የሃገር በቀል የጣውላ ዛፍ ዝርያዎችን ዕድገታቸው በችግኝ ጣቢያ በመገምገም የችግኝ አመራት መመሪያ ማውጣት፣
- የስር ቀስቃሽ ሆርሞኖች በመጠቀም የዝግባ ቁራጭ ስር እንዲያወጣ`በመፈተሽ መረጃ ማውጣት፣
- ዘመናዊ የዛፍ ዘር ኦርቻርድ ማቋቋም፣
- በ5 የዛፍ ዘር ምንጮች ላይ ምርምር ማካሄድ፣

**በስርዓተ-ምህዳር አያያዝ ምርምር**

- የሁለት የተፈጥሮ ደኖች የዕጽዋት አይነት እና ስብጥር መረጃ ለማውጣት የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣
- በሦሥት ደጋማ ደኖች ላይ የሚገኙ 13 የዛፍ ዝርያዎች የአበባ እና የፍሬ ወቅት ጊዜ ጥናት ማካሄድ፣
- የ4 ደጋማ የደን ዝርያዎች ዘር የአበቃቀል ጥናት ማካሄድ፣
- የወራሪ ዕጽዋት በተፈጥሮ ደን ውስጥ የሚገኙትን የዕጽዋት እና የዕንስሳት መኖ ዝርያዎች አይነትና እና ስብጥር ላይ ያለውን ተጽዕኖ የሚያሳይ መረጃ ለማውጣት የሚያስችል ምርምር ማካሄድ፣
- የተቀናጀ የተፋሰስ ስራዎች ሀይቆች ስነ-ምዳር መስተጋብር ላይ የሚያስከትለውን አወንታዊ ተጽዕኖ ለመገምገም የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣
- በተፈጥሮ ደኖች ላይ መረጃዎችን እና ቴክኖሎጂዎችን ለማመንጨት ምርምር ማካሄድ፣
- ወደ ሃይቅ የሚገቡ ንጥረ-ነገሮችን (nutrients) መጠን ሊቀንሱ የሚችሉ አገር በቀል ማክሮፋይቶችና ለአካባቢ ተስማሚ የሆኑ ፈጣን እድገት ያላቸው የዛፍ ዝርያዎች መረጣና ልየታ ማካሄድ፣
- ከከሰል የሚወጣውን የንጥረ ነገርና የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን ማጥናት፣
- ለማገዶ የሚሆኑ የዛፍ ዝርያዎችን ባህሪያት ማጥናት፣
- በተመረጡ የግራር ዛፍ ዝርያዎች ላይ የእድገት እና የአየር ንብረት ዝምድናን ማጥናት፣
- የበረሃማነት ለውጥን ከደን ሽፋን ለዉጥ ጋር በማገኛኘት ጥናት ማካሄድ፣

- የአየር ንብረት ለውጥ በተለያዩ የቢሆንልኝ (scenarios) የወደፊትን የአየር ሁኔታ ከዕጽዋት ሽፋን ጋር በማገናኘት ጥናት ማካሄድ፣
- የመሬት አጠቃቀም ለውጥንና የደን ይዞታን የሚያሳይ ጥናት ማጥናት፣
- እርጥበታማ ደኖች የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ያላቸዉን አስተዋጽኦ ማጥናት፣
- የአየር ንብረት ለውጥ በመጥፋት ላይ ባሉ ሁለት የዛፍ ዝርያዎች እድገት ላይ ያለውን ጫና የሚያሳይ ምርምር ማካሄድ፣
- በተጎዳ መሬት ላይ ባዮቻርን በመጠቀም በችግኝ እድገት እና በአፈር ካርቦን መጠን ላይ ያለውን ፋይዳ ማጥናት፣

## በሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ፣ፖሊሲ ኤክስቴንሽን ምርምር

- የመሬት አጠቃቀምና ሽፋን ከእርሻ ወደ ደን የሚቀየርበትን ዋና ዋና ምክንያት ማጥናት፣
- የመሬት አጠቃቀምና ሽፋን ከደን ወደ እርሻ የሚቀየርበትን ዋና ዋና ምክንያት ማጥናት፣
- የእንጨት ኢንደስትሪዎች ያላቸዉን ውጤታማነትና ትርፋማነት ማጥናት፣
- የተለያዩ የኃይል ቆጣቢ የቴክኖሎጂ አማራጮችን በመጠቀም የደን ሀብትን ከውድመት መጠበቅ የሚያስገኛቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎችን ማጥናት፣
- ከዉጭ የገባዉን ቀርከሃ የቅድመ ማስፋፋት ስራ በተሠራባቸዉ አካባቢዎች የአርሶ አደሮች የቴክኖሎጂ ቅበላ ማጥናት፣
- በተለያዩ የእንጨት ዝሪያዎች የተባይ መከለከያ ዘዴዎችን በመጠቀም ለረጅም ግዜ አገልግሎት የሚሰጡበትን መንገድ ለተለያዩ ባለድርሻ አካለት ማስተዋወቅና የቴክኖሎጂ ቅበላቸዉን ማጥናት፣

## በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር

- በኢትዮጵያ የለማ ለኢንዱስትሪ እና ለኮንስትራክሽ አገልግሎት ሊውል የሚችል የፓይነስ ቴኩማኒ (Pinus tecunumanii) የውጭ ሐገር የዛፍ ዝርያ ጣውላ አውዳሚ ተባዮችን የመቋቋም ብቃት (Durability) እና የአውዳሚ ተባይ መከላከያዎች ጥናት ማካሄድ፣
- ከቆላ ቀርቀሃ ጣውላ (Laminated lumber) ለማምረት የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣
- ከካማልዱለንሲስ ባህርዛፍ እና ከአኬሽያ ዲከረንስ የወለል ንጣፍ (ፓርኬ) ማምረት የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣
- ለኢንዱስትሪ አገልግሎት ሊውሉ በሚችሉ የሁለት ዋና ዋና የዛፍ ዝርያዎች የእምቅታ (Density) ባህርያት የሚያሳይ መረጃ (Density Mapping) ጥናት ማካሄድ፣
- ከደጋ ቀርቀሃና ከሸንኮራ አገዳ ተረፈ-ምርት ፐልፕና ወረቀት ማምረት የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣
- ከሳሊግና ባህርዛፍ (Eucalyptus salgina) ተረፈ- ምርት ለኃይል ምንጭነት የሚውል ፒሌትና ብሪኬት በተለያዩ የማቀነባበሪያ ዘዴ ማምረት የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣

- ከCupressus lustinica ተረፈ-ምርት ለኃይል ምንጭ የሚውል ኢታኖል ማምረት እና የተመረተውን ባዮኢታኖል የጥራት ደረጃ ለማወቅ የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣
- በብዛት ጥቅም ላይ ያልዋሉ የዕጣንና ሙጫ ዛፎች መለየት የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣
- የዕንኮይ ዛፍ እና የጨው ዋንዛ የክምችት ሁኔታ፣ የአበባ ጊዜ እና የፍሬ ምርት መጠን ለማወቅ የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣
- የሞሪንጋ ዛፍ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ያለውን የስርጭት እና የምርት መጠን ማወቅ የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣
- የሞሪንጋ ዛፍ በተለያየ የቁመት መጠን የሚሰጠውን የምርት መጠን ማወቅ የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣
- የሞሪንጋ ዛፍ በተለያዩ ስርዓተ-ምህዳሮች ያለውን የፍሬ ምርታማነት፤ የዘይት ምርት መጠንና ጥራት ጥናት ማካሄድ፣
- የእንጨት ውጤቶች አውዳሚ ተባዮችን የመቋቋም ብቃት እና የመከላከያዎች ውጤታማነት ጥናት ማካሄድ፣
- የዲማ(ባኦባብ)፣ ጊሽጣ፣ የበረሃ ሎሚ፣ እንኮይና ሮቃን የማላመድ ምርምር ሙከራዎች ጥናት ማካሄድ፣
- የቦሶሊያ ፓፕሪፌራ እና ሴኒጋል ግራር  የማድማት ጥናት ማካሄድ፣
- የደጋ፣ የቆላ እና ከውጭ ገብተው የተላመዱ የቀርከሃ ዝርያዎች የማላመድ ጥናት ማካሄድ፣
- የአኬሽያ ካፍራ ጣውላ አውዳሚ ተባዮችን የመቋቋም ጥናት ማካሄድ፣

**ግብ 9. የመረጃና ቴክኖሎጂ ትውውቅና ሽግግርን ማሳደግ**

የሚጠበቅ ውጤት፡ ያደገ የመረጃ እና ቴክኖሎጂ ተደራሽነት

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለ41 የምርምር ውጤቶች የትግበራ ፓኬጅ ማዘጋጀት፣
- አምስት የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና አሰራር ማንዋሎች ማዘጋጀት፣
- በተመረጡ የምርምር ውጤቶች (ቴክኖሎጂዎች) ላይ ለ 200 ተጠቃሚዎች የቴክኖሎጂ ቅድመ ማስፋፋት ስልጠና መስጠት፣
- 22 የምርምር ውጤቶችን በታወቁ ጆርናሎች ላይ ማሳተም፣

**ግብ 10. የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ**

የሚጠበቅ ውጤት፡ ያደገ የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ለ112,500 ወጣቶች እና ለ62,500 ሴቶች የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ማድረግ፣
- የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች አካቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት፣
- 2 የህፃናት ማቆያ ማዘጋጀትና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣

**ግብ 11 የመሰረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ**

የሚጠበቅ ውጤት፡ ያደገ የተቋሙ መሰረተ ልማት

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የደን ዉጤቶች ኢኖቬሽን ላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ G+3 ህንፃ ግንባታ ደረጃን 100% እንዲደርስ ክትትል፣ ድጋፍና እና ቁጥጥር ማድረግ፣
- የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል ላቦራቶሪ ኮምፕክስ G+5 ህንፃ ግንባታን 100% እንዲደርስ ክትትል፣ ድጋፍና እና ቁጥጥር ማድረግ፣
- የተቋሙን ድረ-ገጽ 100 % ወደ portal level ማሳደግ፤
- ብሔራዊ የዛፍ ዘር ምንጮች ፖርታል እና የዛፍ ዘር ትስስር ኔትዎርክ ማስተዳደር እና ማሻሻል፣
- የተቋሙን አሰራር አውቶሜት ማድረግ፣
- 2 የምርምር ሙከራ ጣቢያዎችን ማጠናከር፣
- 371 ሄክታር ነባር የዘር ምንጮችን መንከባከብና ማስተዳደር፣
- 8 የምርምር ችግኝ ጣቢያዎች ማካሄድ፣
- የማዕከላትን የመስክ መሳሪዎች አቅርቦት ማሳደግ፣
- ፓወር ባንክ (UPS) በመጠቀም የተቋሙ የኔትወርክ ችግር መቅረፍ፣

**ግብ 12. የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ፣**

የሚጠበቅ ውጤት፡ ያደገ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም፣

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በሰባት ርዕሰ ጉዳዮች ለ 265 ክልል ባለሙያዎች የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት፣
- ለ164 ተመራማሪዎች የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት፣
- ለ60 አመራሮች የአቅም ግምባታ ስልጠና መስጠት፣
- ሁለት የልምድ ልውውጥ ማካሄድ፣
- የረጅም ጊዜ ስልጠና በሦስተኛ ድግሪ 1 ሰራተኞች ስልጠና እንዲያገኝ ማድረግ፣
- የረጅም ጊዜ ስልጠና ላይ ለሚገኙ 71 የተቋሙ ሰራተኞች ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣

## 11. ተቋማዊ የለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ (የሪፎርም ሥራዎች)

- አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓቱን ሊያግዙ የሚችሉ የውስጥ አሰራር መመሪያዎችን በማዘጋጀት/በመከለስ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ማዘጋጀት/ማሻሻል/መከለስ እና ወደስራ ማስገባት፣
- የተገልጋይ ቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር፣
- ከተገልጋይ የሚቀርቡ አስተያየቶችን መሰብሰብ፣ መተንተንና መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች ካሉ ከመፍትሔ ሃሳብ ጋር ማቅረብ፣
- በተቀመጠው የውጤት ተኮር ዕቅድ መሰረት አፈፃፀምን በየደረጃው መገምገምና ደረጃ ማውጣት፣ የአፈፃፀም ድክመት የሚታይባቸውን ፈፃሚዎች ማብቃት፣ የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ግንባር ቀደም ፈፃሚዎችን መለየትና እውቅና መስጠት፣
- ከመላ ሰራተኛው ጋር በየሶስት ወሩ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- የ15 ቀንና ወርሃዊ የማኔጅመንት ስብሰባ ሳይቆራረጥ እንዲካሄድ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

## 12.ማስፈፀሚያ በጀት

የኢትዮጵያ የደን ልማት በ2015 በጀት ዓመት ስራዎችን ለማከናወን የሚያስፈልግ በጀት ብር 317,047,855.00 (በመደበኛ 187,047,855.00 ብር እና በካፒታል 130,000,000.00 ብር) የተመደበለት ሲሆን በየፕሮግራም ድልድሉ በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል።

| ፕሮግራም ስም | ዓመታዊ የታቀደ በጀት |
|---|---|
| **መደበኛ በጀት** | |
| ፕሮግራም 1፡- አስተዳደርና ስራ አመራር | 35,847,443.00 |
| ፕሮግራም 2.፡- የደን ምርምር ፕሮግራም | 63,610,273.00 |
| ፕሮግራም 3፡- የደን ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ፕሮግራም | 87,590,139.00 |
| **የካፒታል በጀት** | |
| የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል ላቦራቶሪ ሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክት | 80,000,000.00 |
| የደን ወጤቶች ኢኖቬሽን ላቦራቶሪ ሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክት | 50,000,000.00 |
| **ድምር** | **317,047,855.00** |

## የ2015 በጀት ዓመት የካፒታል ፕሮጀክቶች ዓመታዊ የፊዝካል (%) እና ፋይናንስ ዕቅድ /በሚሊዮን ብር/ማቅረቢያ ፎርማት

| የበጀት ኮድ | የፕሮጀክት ስም | የሚሰራት ቦታ | የተጀመረበት ወርና ዓ.ም | የሚጠናቀቅበት ወርና ዓ.ም | | የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ወጪ | | የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ዕቅድ (%) | እስከ 2014 መጨረሻ የተሰራ የፊዚካል ሥራዎች (%) | የ2015 በጀት ዓመት የፕሮጀክቱ የፊዝካል ዕቅድ (%) | የ2015 በጀት ዓመት የፕሮጀክቱ የፊይናንስ ዕቅድ (በሚ/ን ብር) | የ2015 ዓ.ም የፊዚካል ሥራዎች ዕቅድ በሩብ ዓመት (%) | | | | የ2015 ዓ.ም የፋይናንስ ዕቅድ በሩብ ዓመት (በሚ/ን ብር) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በመጀመሪያው ዕቅድ /Original | በተስተካከለው ዕቅድ (ዕቅዱ ከተሸሻለ) /Revised | በመጀመሪያ ዕቅድ | በተሸሻለው ዕቅድ (ዕቅዱ ከተሸሻለ) | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል የላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ ህንፃ ግንባታ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል | ሃምሌ 2011 | ሰኔ 2012 | 2015 | 352.397 | 469.333 | 30 | 15 | 100 | 80 | 25 | 40 | 70 | 100 | 40 | 40 | | |
| | የደን ውጤቶች ማዕከል የላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ ህንፃ ግንባታ | የደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ማዕከል | ሃምሌ 2011 | ሰኔ 2012 | ሰኔ 2014 | 174.015 | 154.765 | 100 | 40 | 100 | 50 | 50 | 60 | 80 | 100 | 30 | 20 | | |
| | | | | | | 526.412 | 624.098 | | | | 130 | | | | | 70 | 60 | | |

*ለሁለቱም የላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ ህንፃ ግንባታ በበጀት ዓመቱ የሚያስፈልገው በጀት በተጠየቀው መሰረት በቂ በጀት አልተመደበም፡፡

## 13.የክትትልና ግምገማ ስርዓት

ውጤታማ የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት የፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ደረጃ ለማሻሻል እና የሚጠበቁ ውጤቶች መምጣታቸውን ለማረጋገጥ ዋነኛ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በመሆኑም የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ለመከታተል፣ ለመገምገምና እንደ አስፈላጊነቱ የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል የድጋፍ ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዕቅድ አስፈጻሚ እና ፈፃሚ አካላት ዘንድ የግልፀኝነት እና የተጠያቂነት አሰራር በማስፈን ድክመቶች እንዲታረሙና ጥንካሬዎች እንዲጎለብቱ ይደረጋል፡፡ ይህም የሚረጋገጠው በየደረጃው በሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች የሩብ አመትና አመታዊ አፈጻጸምን በመገምገም እንዲሁም በየደረጃው ባሉ አመራሮችና ቡድኖች የመስክ ክትትልና ግምገማ በማድረግ፣ ይሆናል፡፡

በየ15 ቀኑ፣ በየወሩና በየሩብ ዓመቱ በዋናው መስሪያቤትና በማዕከላት የማኔጅመንት ስብሰባ በመወያየትና ስራዎች በዕቅድ መሰረት መከናወናቸውን በመከታተል በትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች የሚፈቱበት አሰራር ይጠናከራል፡፡ በየደረጃው በሚካሄደው ክትትልና ግምገማ የሚገኙ መረጃዎች ተተንትነው በሪፖርት ለማኔጅመንቱ ይቀርባሉ፤ ማኔጅመንቱ በሚወስናቸው ውሳኔዎች እና በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፣ ተገቢ ድጋፍና እገዛ ይደረጋል፣ ለሚመለከታቸውም አካላት ግብረ-መልሶች ይሰጣሉ፡፡ ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረኮች ይከናወናሉ፡፡ በተለያየ ደረጃ ባሉ የክትትልና ግምገማ ቡድኖች የመስክ ክትትልና ግምገማ ይካሄዳል፡፡ ይህንንም የሚያግዝ የተቋሙ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ጋድላይን/መመሪያ ይዘጋጃል/ይሻሻላል፡፡

በአጠቃላይ ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት በዕቅድ ዘመኑ የተያዙ ግቦች እንዲሳኩ ተገቢ ክትትል፣ ድጋፍና እገዛ ይደረጋል፡፡

## 14.ማጠቃለያ

በታቀደው የበጀት ዓመት ችግር ፈቺ የደን ምርምርና ተቋማዊ አቅም ግንባታ እና ዘላቂ የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ፣ እንክብካቤና አጠቃቀም በማካሄድ የደን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስርዓተ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ ለማሳደግ ሰፊ ስራ ለመስራት ታቅዷል፡፡ በመሆኑም የፊዚካልና የፋይናንስ አፈፃፀም በየደረጃው ወቅቱን ጠብቆ በመገምገም በበጀት ዓመቱ የሚጠበቁ ውጤቶች በዕቅዱ መሰረት መከናወናቸውን በማረጋገጥና ተገቢውን የአፈፃፀም ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ይቀርባል፡፡

## 15.ዝርዝር የውጤት አመላካቾችና ዒላማዎች (የድርግት መርሃ ግብር)

### የ2015 በጀት ዓመት ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች አመልካቾች መለኪያዎች እና ዒላማዎች መርሃ ግብር

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 በጀት አመት ኢላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| ተገልጋይ | **ግብ 1. የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ** | | | | | | | | |
| | ያደገ የተገልጋይ እርካታ | በመቶኛ | 84 | 90 | | 86 | 88 | 90 | |
| | በአገልግሎት አሰጣጥ ለሚነሱ ቅሬታዎች የተሰጠ ምላሽ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | |
| | የተገልጋይ እርካታን ደረጃ ለማወቅ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት | በቁጥር | 1 | 1 | | | | 1 | |
| ፋይናንስ | **ግብ 2. የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ** | | | | | | | | |
| | ጥቅም ላይ የዋለ በጀት ድርሻ | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | |
| | በኦዲት ግኝት ላይ የተወሰደ ማስተካከያ እርምጃ | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | |
| | የተደረገ የውስጥ ኦዲት ክትትል | በቁጥር | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | የኦዲት ግኝቶች መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ የማስተካከያ መርሃ ግብር | በቁጥር | 1 | 1 | | | 1 | | |
| | **ግብ 3. የሀብት ግኝትን ማሳደግ** | | | | | | | | |
| | ከአጋር ሀገሮች እና ድርጅቶች የተገኘ የፋይናንስ ድጋፍ | በሚሊየን ዶላር | | 30 | 20 | | 10 | | |
| | ከዛፍ ዘርና ተረፈ ምርት ሽያጭ የተገኘ ገቢ | በሚ/ብር | 0.78 | 1 | | 0.5 | 0.4 | 0.1 | |
| የውስጥ አሰራር | **ግብ4. ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል** | | | | | | | | |
| | ከደን ዘርፍ የተቀነሰ የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት መጠን | በሚ/ቶን | 10.2 | 7 | | | | 7 | |
| | የደን ሽፋን ልኬት መረጃ | በቁጥር | 1 | 1 | | | | 1 | |
| | ተሳትፎ የተደረገባቸው አለም አቀፍ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ መድረኮች | ቁጥር | 2 | 2 | | 1 | | 1 | |
| | **ግብ 5. የደን ህግ ተከባሪነት ማረጋገጥ** | | | | | | | | |
| | የተዘጋጁ የደን ህግ ማዕቀፎች | በቁጥር | - | 4 | | 1 | 2 | 1 | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 በጀት አመት ኢላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ለመፍጠር የተዘጋጁ መድረኮች | በቁጥር | - | 3 | | 1 | 2 | | |
| | በደን ህጎች እና አፈፃፀም ላይ ግንዛቤ ያገኙ የህብረተሰብ ክፍል ብዛት፣ | በሚሊዮን ቁጥር | 2.1 | 2.5 | | | 2 | 0.5 | |
| | የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው በደን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ብዛት | በቁጥር | 100 | 400 | 75 | 125 | 125 | 75 | |
| | የደን እሳት በብዛት የሚከሰትባቸው ቦታዎች (hot spot area) የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | ህገወጥ የደን ውጤቶች ዝውውር የሚበዛባቸው የተለዩ አካባቢዎች (hot spot area) የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | ህገወጥ የደን ጭፍጨፋ የሚበዛባቸው የተለዩ አካባቢዎች (hot spot area) የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | **ግብ 6. አገራዊ የደን ሽፋንን ማሳደግ ፣** | | | | | | | | |
| | በደን የተሸፈነ መሬት ድርሻ | በመቶኛ | 17.2 | 20 | | | | 20 | |
| | ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ የዛፍ ዘር መጠን | በቶን | 504.8 | 200 | 20 | 130 | 50 | - | |
| | ወደ ዛፍ ዘር ስርዓት ያልገቡ እና ዕጥረት ያለባቸው ወደ ዛፍ ስርዓት የቀረቡ የዛፍ ዝርያዎች ብዛት | ቁጥር | | 15 | 3 | 5 | 5 | 2 | |
| | የተዘጋጁ ችግኞች ብዛት | ቁጥር (በቢሊዮን) | **3.79** | 3 | - | 0.25 | 1 | 1.75 | |
| | የተጠበቀ ነባር፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ደን መሬት ስፋት | ሄ/ር (በሚሊዮን) | 19.2 | 19.2 | 19.2 | 19.2 | 19.2 | 19.2 | |
| | የተተከሉ ችግኞች አማካይ የፅደቀት ምጣኔ | በመቶኛ | 83.5 | 85 | | 85 | | 85 | |
| | የዛፍ ተከላ የተካሄደበት መሬት ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 0.699 | 0.6 | 0.6 | | | | |
| | እንዲያገግም የተደረገ የተራቆተ የደን መሬት ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 0.692 | 1 | | 0.25 | 0.5 | 0.25 | |
| | በቀርከሀ ደን እንዲለማ የተደረገ መሬት ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 0.067 | 0.02 | 0.02 | | | | |
| | ለደን ሀብት ቆጠራ (Forest inventory) የተወሰደ ናሙና | በመቶኛ | - | 50 | | 10 | 30 | 10 | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 በጀት አመት ኢላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | የደን ማኔጅመንት ፕላን የተዘጋጀላቸው ደኖች ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 0.194 | 0.2 | | | 0.075 | 0.125 | |
| | የደን አያያዝ የተሻሻለላቸው የከተሞች ብዛት | በቁጥር | 9 | 5 | 1 | 2 | 1 | 1 | |
| | የጥምር ደን ግብርና ስራ እንዲጎለብት የተደረገበት የመሬት ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | | 0.1 | | | | 0.1 | |
| | የደን እሳት መንስኤዎችን መለየት፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያና መከላከያ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል ማንዋል | በቁጥር | | 2 | | | 1 | 1 | |
| | የደን እሳት ቃጠሎ ለመቆጣጠር እንዲቻል ግብረ ሃይል እንዲደራጅ እና እንዲጠናከር የተደረገ ክትትል እና ድጋፍ | በቁጥር | | 4 | | 4 | | | |
| | የደን ሃብትን የሚያጠቁ የመጤ እና ወራሪ የዛፍ ዝርያ አረሞችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የተዘጋጀ ማንዋል | በቁጥር | | 1 | | | 1 | | |
| | ለደን ተባይ በሽታ ቅድመ መከላከል እና መቆጣጠር የተዘጋጀ ማንዋል | በቁጥር | | 1 | | 1 | | | |
| | የተዘጋጀ የደን ማኔጅመንት ፕላን መመሪያ (Guideline) | በቁጥር | | 1 | | | 1 | | |
| | **ግብ 7. የደን ልማት ለአገራዊ የኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን ድርሻ ማሳደግ፣** | | | | | | | | |
| | ነባር የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገለት የተፈጥሮ ደን ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 2.16 | 2.16 | 2.16 | 2.16 | 2.16 | 2.16 | |
| | አዲስ የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገለት የተፈጥሮ ደን ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | - | 0.2 | - | - | 0.1 | 0.1 | |
| | ከሰው ሰራሽ ደንና ከደን ተረፈ ምርቶች በተሻሻለ ዘዴ የተመረተ ከሰል መጠን | ሚሊ/ቶን | 0.345 | 0.2 | - | 0.067 | 0.067 | 0.066 | |
| | ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የቀረበ የደን ምርት መጠን | ቶን (ሚሊዮን) | 2.34 | 1.02 | - | 0.34 | 0.34 | 0.34 | |
| | በደን ዘርፍ ስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ብዛት | በሚሊዮን ቁጥር | 0.255 | 0.25 | 0.02 | 0.1 | 0.1 | 0.03 | |
| | ሥርዓተ ምህዳሮች የሚያመነጩትን አገልግሎት ዋጋ ትመና የሚያሳይ መረጃ፣ | በቁጥር | - | 1 | - | - | - | 1 | |
| | ከደን ሮያሊቲ የተገኘ ሀብት መጠን | በሚሊዮን ብር | 293.1 | 250 | 50 | 60 | 70 | 70 | |
| | ከደን ምርት ኤክስፖርት የተገኘ እና በሃገር ውስጥ የደን ምርት ምክንያት የዳነ የውጭ ምንዛሪ መጠን | በሚሊዮን ዶላር | | 20 | 2 | 5 | 6 | 7 | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 በጀት አመት ኢላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | ኑሮአቸውን በደን ላይ መሰረት ያደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎች መጠን የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | - | 1 | - | - | 1 | - | |
| | የደን ሃብት ለሃገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ለማወቅ የሚያስችል የወጣ መረጃ | በቁጥር | - | 1 | | | | 1 | |
| | የደን ኢንተርፕራይዞችን እና ኢንዱስትሪዎችን ያለባቸውን ችግሮች ለመለየትና ለመደገፍ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ | በቁጥር | - | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | **ግብ 8. የደን መረጃና ቴክኖሎጂ ማመንጨትና ማላመድ** | | | | | | | | |
| | **በምርምር የወጡ ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎች** | | | | | | | | |
| | **ቴክኖሎጂዎች** | **በቁጥር** | 6 | 6 | - | - | - | 6 | |
| | **መረጃዎች** | **በቁጥር** | 31 | 42 | - | 7 | 6 | 29 | |
| | **ድምር** | **በቁጥር** | 37 | 48 | - | 7 | 6 | 35 | |
| | **በሂደት ላይ ያሉ የምርምር ስራዎች ብዛት** | **በቁጥር** | 70 | 104 | 104 | 104 | 104 | 104 | |
| | **በሰው ሰራሽና ጥምር ግብርና ደን ምርምር** | | | | | | | | |
| | የኦሜድላ እና የዴክረንስ ግራር መሠረት ባደረገ የጥምር ደን ግብርና ሞዴል ላይ የወጣ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የማህበረተሰቡን የፍራፍሬ ዛፍ ፍላጎት የሚያሳይ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የጥምር ደን ግብርና አሰራሮችን የሚያሻሽሉ የምርምር ስራዎች ብዛት | ቁጥር | 29 | 20 | 20 | 20 | 20 | 20 | |
| | ለጣዉላ በሚዉሉ የሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎች የመጀመሪያ የመትከያ ርቀት በእድገት መጠን ላይ ያለዉ አስተዋጽኦ የሚያሳይ መረጃ | ቁጥር | | 2 | | | | 2 | |
| | የነጭ ባህር ዛፍ የመትከያ ርቀት በእድገት መጠን እና በእንጨት ባህሪይ ላይ ያለዉ አስተዋጽኦ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | 1 | | |
| | የቀረሮ ዛፍ በቁርጥራጭ የሚባዛበት ዘዴ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | 1 | | | |
| | የጥቁር እንጨት እድገት ሙከራ ብዛት | ቁጥር | | 1 | 1 | | | | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 በጀት አመት ኢላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | የማህበረሰብ የችግኝ ፍላጎትን በአይነት እና በመጠን በመለየት የወጣ መረጃ | ቁጥር | | 3 | | 3 | | | |
| | የሰው ሰራሽ ደን የምርምር ስራዎች ብዛት | ቁጥር | 31 | 24 | 24 | 24 | 24 | 24 | |
| | በተራቆቱ እርጥበት አጠር መሬቶች የችግኝ እድገትን ሊያሻሽል የሚችሉ የአተካከል ዘዴዎች ላይ የወጣ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | ውርጭ በሚበዛባቸው ከፍተኛ ቦታዎች ላይ አዲስ የተቋቋሙ የችግኝ አፀዳደቅ ሙከራዎች ብዛት | ቁጥር | 2 | 3 | 3 | | | | |
| | በወንዝ ዳርቻ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚሳይ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | 1 | | |
| | በወንዝ ዳርቻ የሚገኙ የዛፍ እና የቁጥቋጦ ዝርያዎችን ስብጥር የሚያሳይ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | 1 | | |
| | በዛፍ የታገዘ የተፋሰስ አያያዝ እና የተጎዱ መሬቶች ማገገሚያ የምርምር ስራዎች ብዛት | ቁጥር | 7 | 9 | 9 | 9 | 9 | 9 | |
| | **በደን አጠባበቅ ምርምር** | | | | | | | | |
| | የዛፍ ዝርያዎችን የሚያጠቁ ነፍሳተ ተባይ ላይ የተካሄዱ የምርምር ስራዎች ብዛት | በቁጥር | | 4 | **4** | 4 | 4 | **4** | |
| | በዛፍ በሽታዎች ላይ የተካሄዱ የምርምር ስራዎች ብዛት | በቁጥር | | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | የተፈጥሮ ደን ቦታዎች የእሳት ቀጠና፣ ባህርይ እና ጸባይ/ሁኔታ ለማወቅ የተካሄዱ የምርምር ስራዎች ብዛት | በቁጥር | | 1 | **1** | 1 | 1 | 1 | |
| | **በዛፍ ዘር ቴክኖሎጅ ምርምር** | | | | | | | | |
| | የቅድመ መዝራት የዘር ባህሪ የሚያሳይ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | በችግኝ ጣቢያ ዕድገታቸው የተገመገሙና የችግኝ አመራት መመሪያ የወጣላቸው አገር በቀል የጣውላ ዛፍ ዝርያዎች ብዛት | ቁጥር | | 2 | | | | 2 | |
| | ሆርሞኖች በመጠቀም የዝግባ ቁርጥራጮችን የማባዛት ዘዴ የሚያሳይ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የተቋቋመ ዘመናዊ የዛፍ ዘር ኦርቻርድ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 በጀት አመት ኢላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | የዛፍ ዘር ምንጭ ሙከራዎች ብዛት | ቁጥር | | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | |
| | **በስርዓተ-ምህዳር አያያዝ ምርምር** | | | | | | | | |
| | የተፈጥሮ ደን ውስጥ የሚገኙ የዕጽዋት አይነትና ስብጥር የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | 1 | | | |
| | የ13 ዛፍ ዝርያዎች የአበባ እና የፍሬ ወቅት ጊዜ የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የ4 ዛፍ ዝርያዎች የዘር የአበቃቀል ባህሪ የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | 1 | | | |
| | የወራሪ ዕጽዋት በተፈጥሮ ደን ውስጥ ያለውን ተጽዕኖ የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የተቀናጀ የተፋሰስ ስራዎች በዝዋይ እና ጣና ሀይቆች ስነ-ምዳር መስተጋብር ላይ የሚያስከትለውን አወንታዊ ተጽዕኖ ለመገምገም የሚያስችል የተካሄደ የምርምር ሙከራ ብዛት | ቁጥር | | 8 | 8 | 8 | 8 | 8 | |
| | በተፈጥሮ ደኖች ምርምር በማካሄድ የተለያዩ መረጃዎችን እና ቴክኖሎጂዎችን ለማመንጨት የተካሄደ የምርምር ሙከራ ብዛት | ቁጥር | | 17 | 17 | 17 | 17 | 17 | |
| | የወራሪ ዕጽዋት በተፈጥሮ ደኖች ላይ ያስከተለውን ተጽዕኖ የሚያሳይ መረጃ እና የወራሪ ዕጽዋቶች ለመቆጣጠር የሚያስችል ቴክኖሎጂ ለማመንጨት የተካሄደ የምርምር ሙከራ ብዛት | ቁጥር | | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | ለሃይቅ ውሃ ጥራት መጠበቂያ የሚውሉ የማክሮፋይቶችና የዛፍ ዝርያዎችን ልየታ የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | ከሰል በማመረት ሂደት ውስጥ የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዝና ንጥረ ነገርን የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | 1 | | | |
| | ለማገዶ የሚሆኑ ጥናት የተደረገላቸው 4 የዛፍ ዝርያዎች መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | 1 | | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 በጀት አመት ኢላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | በተጎዳ መሬት ላይ ባዮቻርን በመጠቀም በችግኝ እድገት እና በአፈር ር ካርቦን መጠን ላይ ያለውን ፋይዳ ለማወቅ የተካሄደ የምርምር ሙከራ ብዛት | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | የበረሃማነት ለዉጥ ከደን ሽፋን ለዉጥ ጋር ያለውን ትስስር የሚያሳይ የወጣ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | በላይኛዉ አዋሽ ተፋሰስ ላይ የመሬት አጠቃቀም  እና የደን ሽፋን ለዉጥን የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | 1 | | |
| | የአየር ንብረት ለዉጥ  በዕጽዋት ሽፋን ላይ ያለውን ተፅዕኖ የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የእርጥበታማ ደኖች የአየር ንብረት ለዉጥን ለመቋቋም ያላቸዉን አስተዋጽኦ የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | አየር ንብረት ለውጥ በመጥፋት ላይ ባሉ ሁለት የዛፍ ዝርያዎች እድገት ላይ ያለውን ጫና የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | 1 | | |
| | የአየር ንብረት ለውጥ በተመረጡ የግራር ዛፍ ዝርያዎች እድገት ላይ ያለውን ተጽዕኖ የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | **የሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ፤ፖሊሲ ኤክስቴንሽንና ምርምር** | | | | | | | | |
| | በተመረጡ ቦታዎች ከእርሻ ወደ ደን የሚቀየርበትን ዋና ዋና ምክንያት የሚያሳይ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የመሬት አጠቃቀምና ሽፋን ከደን ወደ እርሻ የሚቀየርበትን ዋና ዋና ምክንያት የሚያሳይ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የእንጨት ኢንደስትሪዎች ያላቸዉን ዉጤታማነትና ትርፋማነት የሚያሳይ  መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የኃይል ቆጣቢ የቴክኖሎጂ አማራጮችን በመጠቀም የደን ሀብትን ከዉድመት መጠበቅ የምያስገኛቸዉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎችን የሚያሳይ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 በጀት አመት ኢላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | ከዉጭ የገባዉ ቀርከሃ ቴክኖሎጂ የማስተዋወቅ ስራ ላይ የተጠቃሚዎችን ዕዉቀት፣ አመለካከት እና ለመተግበር ያላቸዉን ፍላጎት የሚያሳይ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የተለያዩ የእንጨት ዝሪያዎች ለረጅም ግዜ አገልግሎት የሚሰጡበትን ቴክኖሎጂ ለተጠቃሚዎች በማስተዋወቅ የተጠቃሚዎችን ዕዉቀትና አመለካከት የሚያሳይ መረጃ | ቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | **በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር** | | | | | | | | |
| | የቴኩማኒ ፓይን ጣውላ አውዳሚ ተባዮችን የመቋቋም ባህሪ/አቅም የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | ከቆላ ቀርከሐ ጣውላ ማምረት የሚያስችል ቴክኖሎጂ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | ከካማልዱለንስስ ባህርዛፍ እና ከአኬሽያ ዲከረንስ የወለል ንጣፍ (ፓርኬ) ማምረት የሚያስችል ቴክኖሎጂ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የሁለት ዋና ዋና የዛፍ ዝርያዎች በተለያየ ስርአተምህዳር ያላቸውን የእምቅታ (Density) ባህርያት የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 2 | | | | 2 | |
| | ከደጋ ቀርከሐ እና ከሻንኮራ አገዳ ተረፈ-ምርት ፕልፕና ወረቀት ማምረት የሚያስችል ቴክኖሎጂ | በቁጥር | | 2 | | | | 2 | |
| | ከሳሊግና ባህርዛፍ ተረፈ-ምርት ለኃይል ምንጭነት የሚውል ፒሌትና ብሪኬት ማምረት የሚያስችል ቴክኖሎጂ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | ከፈረንጅ ጽድ ተረፈ-ምርት ለኃይል ምንጭ የሚውል ኢታኖል ማምረት የሚያስችል ቴክኖሎጂ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | በብዛት ጥቅም ላይ ያልዋሉ የዕጣንና ሙጫ ዛፎች መለየት የሚያስችል መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የዕንኮይ ዛፍ እና የጨው ዋንዛ በተመረጡ ቦታዎች ያላቸውን የክምችት ሁኔታ፣ የአበባ ጊዜ እና የፍሬ ምርት መጠን ማወቅ የሚያስችል መረጃ | በቁጥር | | 2 | | | | 2 | |
| | የሞሪንጋ ዛፍ በተለያዩ ስርአተምህዳር ያለውን የስርጭት እና የምርት መጠን ማወቅ የሚያስችል መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 በጀት አመት ኢላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | የሞሪንጋ ዛፍ በተለያየ የቁመት መጠን የሚሰጠውን ምርት ማወቅ የሚያስችል መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የሞሪንጋ ዛፍ በተመረጡ ቦታዎች ያለውን የፍሬ ምርት፤የዘይት ጥራት እና መጠን የሚያሳይ መረጃ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | የዲማ(ባኦባብ)፣ ጊሽጣ፣ የበረሃ ሎሚ፣ እንኮይና ሮቃ ዝርያዎችን የማላመድ ሙከራዎች ብዛት | በቁጥር | | 3 | | | 1 | 2 | |
| | የቦሶሊያ ፓፕሪፌራ እና ሴኒጋል ግራር የማድማት ሙከራዎች ብዛት | በቁጥር | | 2 | | | 1 | 1 | |
| | የደጋ፣ የቆላ እና ከውጭ የገቡ የቀርከሃ ዝርያዎች የማላመድ ሙከራዎች ብዛት፣ | በቁጥር | | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | የአኬሽያ ካፍራ ጣውላ አውዳሚ ተባዮችን የመቋቋም ምርምር ሙከራዎች ብዛት፣ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | ግብ 9. የመረጃና ቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ | | | | | | | | |
| | **የተዘጋጁ የምርምር ውጤቶች የትግበራ ፓኬጅ ብዛት** | **በቁጥር** | | **41** | | | | **41** | |
| | በሰው ሰራሽ እና ጥምር ግብርና ደን | በቁጥር | | 10 | | | | 10 | |
| | በስርዓተ-ምህዳር (ተፈጥሮ ደን) | በቁጥር | | 8 | | | | 8 | |
| | በአየር ንብረት ሳይንስ | በቁጥር | | 5 | | | | 5 | |
| | በሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ፣ ፖሊሲ ኤክስቴንሽን | በቁጥር | | 7 | | | | 7 | |
| | የዛፍ ዘር ቴክኖሎጂ | በቁጥር | | 2 | | | | 2 | |
| | የደን ውጤቶች ኢኖቬሽን | በቁጥር | | 8 | | | | 8 | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 በጀት አመት ኢላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የደን አጠባበቅ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | **በታወቁ ጆርናሎች ላይ የታተሙ የምርምር ውጤቶች** | **በቁጥር** | | **22** | | | **6** | **16** | |
| | በሰው ሰራሽ እና ጥምር ግብርና ደን | በቁጥር | | 5 | | | | 5 | |
| | በስርዓተ-ምህዳር (ተፈጥሮ ደን) | በቁጥር | | 7 | | | 3 | 4 | |
| | በሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ፣ ፖሊሲ | በቁጥር | | 3 | | | 1 | 2 | |
| | የዛፍ ዘር ቴክኖሎጂ | በቁጥር | | 3 | | | 1 | 2 | |
| | የደን ውጤቶች | በቁጥር | | 3 | | | 1 | 2 | |
| | የደን አጠባበቅ | በቁጥር | | 1 | | | | 1 | |
| | **ተጠቃሚዎች በቴክኖሎጂ ቅድመ ማስፋፋት የተሰጠ ስልጠና** | **በተሳታፊ ቁጥር** | | **200** | | | **100** | **100** | |
| | **ግብ 10. የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ** | | | | | | | | |
| | የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሴቶች ቁጥር | በቁጥር (ሚሊዮን) | 0.072 | 0.063 | 0.009 | 0.0135 | 0.031 | 0.009 | |
| | የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ወጣቶች ቁጥር | በቁጥር (ሚሊዮን) | 0.122 | 0.125 | 0.1 | 0.05 | 0.05 | 0.015 | |
| | የተዘጋጀ የህፃናት ማቆያ | በቁጥር | | 2 | | | 1 | 1 | |
| | የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች አካቶ የተሰጠ ሥልጠናዎች ብዛት | በቁጥር | | 2 | | 1 | | 1 | |
| መማማርና ዕድገት | **ግብ 11. የዘርፉን የመሰረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ፣** | | | | | | | | |
| | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል G+5 ላቦራቶሪ ግንባታ ስራ ያለበት ደረጃ | በመቶኛ | 15 | 100 | 25 | 40 | 70 | 100 | |
| | የደን ዉጤቶች እናቬሽን ማዕከል ላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ G+3 | በመቶኛ | 40 | 100 | 50 | 60 | 80 | 100 | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 በጀት አመት ኢላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | ግንባታ ስራ ያለበት ደረጃ | | | | | | | | |
| | የተጠናከሩ የምርምር ሙከራ ጣቢያዎች ብዛት | በቁጥር | | 2 | | 2 | | | |
| | እንክብካቤ የተደረገላቸው ነባር የዛፍ ዘር ምንጮች | በሄክታር | 371 | 371 | 371 | 371 | 371 | 371 | |
| | የመስክ መሳሪዎች አቅርቦት ፣ እድገት | ቁጥር | | 120 | | 120 | | | |
| | • ካሊፐር ትልቁ | ቁጥር | | 30 | | 30 | | | |
| | • ካሊፐር ትንሹ | ቁጥር | | 10 | | 10 | | | |
| | • ጂፒኤስ | ቁጥር | | 20 | | 20 | | | |
| | • ክሊኖሜትር | ቁጥር | | 20 | | 20 | | | |
| | • ሜትር | ቁጥር | | 20 | | 20 | | | |
| | • ዲያሜትር ቴፕ | ቁጥር | | 20 | | 20 | | | |
| | የሰረቨር ፓወር ባንክ (UPS) | ቁጥር | | 2 | | 2 | | | |
| | ወደ portal level ያደገ የተቋሙን ድረ-ገጽ | በመቶኛ | | 100 | | | | 100 | |
| | አውቶሜት የተደረገ የተቋሙን አሰራሮች | በቁጥር | | 1 | | 1 | | | |
| | የተሻሻለ የዛፍ ዘር ምንጮች ፖረታል እና የዛፍ ዘር ትስስር ኔትዎርክ | በቁጥር | | 2 | | | 2 | | |
| | በመካሄድ ላይ የሚገኙ የምርምር ችግኝ ጣቢያዎች ብዛት | ቁጥር | 8 | 8 | 8 | 8 | 8 | 8 | |
| | ግብ 12. የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ፣ | | | | | | | | |
| | የአጭር ጊዜ ስልጠና ያገኙ ሰራተኞች | በቁጥር | | 265 | | 165 | 100 | | |
| | የአጭር ግዜ ስልጠና ያገኙ ተመራማሪዎች | በቁጥር | | 164 | | 164 | | | |
| | የረጅም ጊዜ ስልጠና ላይ የሚገኙ ሠራተኞች<br>የመጀመሪያ ዲግሪ | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |

| ዕይታ | የአፈጻጸም አመልካቾች | | መለኪያ | መነሻ 2014 | የ2015 በጀት አመት ኢላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | | በሁለተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | 48 | 48 | 48 | 48 | 48 | |
| | | በሶስተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | 25 | 25 | 25 | 25 | 25 | |
| | ስልጠና ያገኙ አመራሮች ብዛት | | ቁጥር | | 60 | | 60 | | | |
| | የተካሄደ የልምድ ልውውጥ ብዛት | | በቁጥር | 1 | 2 | | 1 | 1 | | |

## 16.ዕዝል

### ዕዝል 1. የ2015 በጀት ዓመት የክትትልና ግምገማ መርሃ ግብር

| ተ | የሚከናወኑ ተግባራት | 2015 በጀት ዓመት |
|---|---|---|

| ቁ | | ሐምሌ | | | | ነሐሴ | | | | መስከረም | | | | ጥቅምት | | | | ኅዳር | | | | ታህሳስ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሳምንት | | | | ሳምንት | | | | ሳምንት | | | | ሳምንት | | | | ሳምንት | | | | ሳምንት | | | |
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1 | በዳይሬክቶሬቶች ደረጃ የወርሃዊ የዕቅድ/ስራ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ |
| 2 | የተቋሙ ማኔጅመንት በየ15 ቀን ውይይት ማካሄድ | | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | |
| 3 | በዳይሬክቶሬት ደረጃ የክትትልና ግምገማ ቡድን የሩብ ዓመት የመስክ ክትትልና ግምገማ ማካሄድ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | በተቋሙ የክትትልና ግምገማ ቡድን በየሩብ ዓመቱ/ በስድስት ወር የመስክ ክትትልና ግምገማ ማካሄድ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | የተቋሙን የሩብ ዓመት አፈፃፀም (ከማዕከላትና ክልሎችን የሚመለከታቸው አካላት ጋር) ግምገማ ማካሄድ | ✓ | | | | | | | | | | | | ✓ | | | | | | | | | | | |
| 6 | ከተቋሙ አጠቃላይ ሠራተኛ ጋር የተቋሙን የስድስት ወር አፈፃፀም መገምገም፣ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 7 | በአገልግሎት አሰጣጥና መልካም አስተዳደር ስራዎችን ላይ በየወሩ/በየ3 ወሩ መላው ሰራተኞች ባሉበት መድረክ መገምገም | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ |

| ቁ | | ጥር | | | | የካቲት | | | | መጋቢት | | | | ሚያዚያ | | | | ግንቦት | | | | ሰኔ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሳምንት | | | | ሳምንት | | | | ሳምንት | | | | ሳምንት | | | | ሳምንት | | | | ሳምንት | | | |
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1 | በዳይሬክቶሬቶች ደረጃ የወርሃዊ የዕቅድ/ስራ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ |
| 2 | የተቋሙ ማኔጅመንት በየ15 ቀን ውይይት ማካሄድ | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | | ✓ | |
| 3 | በዳይሬክቶሬት ደረጃ የክትትልና ግምገማ ቡድን የሩብ ዓመት የመስክ ክትትልና ግምገማ ማካሄድ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | በተቋሙ የክትትልና ግምገማ ቡድን በየሩብ ዓመቱ/ በስድስት ወር የመስክ ክትትልና ግምገማ ማካሄድ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | የተቋሙን የሩብ ዓመት አፈፃፀም (ከማዕከላትና ክልሎችን የሚመለከታቸው አካላት ጋር) ግምገማ ማካሄድ | ✓ | | | | | | | | | | | | ✓ | | | | | | | | | | | |
| 6 | ከተቋሙ አጠቃላይ ሠራተኛ ጋር የተቋሙን የስድስት ወር አፈፃፀም መገምገም፣ | | ✓ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | ✓ | |
| 7 | በአገልግሎት አሰጣጥና መልካም አስተዳደር ስራዎችን ላይ በየወሩ/በየ3 ወሩ መላው ሰራተኞች ባሉበት መድረክ መገምገም | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ | | | | ✓ |